# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 240616

ሕዳር 28 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ ገበሬ ገኔቦ

2. አቶ ተስፋዬ ከተማ

3. ወ/ሮ ብርቱካን ከተማ

4. አቶ ታረቀኝ ከተማ

5. አቶ ይስማ ከተማ

6. ወ/ሮ ሸዋዬ ከተማ

7. አቶ ሰለሞን ከተማ

8. አቶ ተስፋሚካኤል ከተማ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ዳመነች ደስታ

2. ወ/ሮ ጥሩወርቅ ከተማ

3. አቶ መልካሙ ከተማ

4. አቶ በለጠ ከተማ -ቀረቡ

5. አቶ ማርቆስ ከተማ -ቀረቡ

6. አቶ ምህረት ከተማ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

7. አቶ ዘሪሁን ከተማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በስር ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፤ ቀሪዎቹ አመልካቾች እና ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገቦች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች መስከረም 05 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአሁን 1ኛ አመልካች ባለቤት እና የ2ኛ አመልካች አባት የሆኑት አቶ ከተማ ጨንጎ ነሀሴ 18 ቀን 2009 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ 1ኛ አመልካች ሚስትነታቸውን፣ 2ኛ አመልካች ልጅነታቸውን እና ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ የሟች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲቀርብ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪም ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ/ም ተጽፎ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ከሟች ጋር ጋብቻ መስርተን እስከ ዕለተ ሞታቸው ኖረናል፤ በጋራ ስንኖር ንብረት አፍርተን ሟች ኑዛዜ ስላደረጉ ውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ንብረት እንዲጣራ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጣልቃ ገቦች ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው እንዲገቡ ተወስኗል፡፡

የውርስ አጣሪ ተመድቦ ግራ ቀኙ ሊጣራልን ይገባል ያሉትን የንብረት ዝርዝር አቅርበው ውርስ አጣሪው የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ/ም ባቀረቡት የውርስ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡ አጣሪው ከኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 096 በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን አረጋግጦ በአሁን 1ኛ ተጠሪ 2 የጋብቻ ማስረጃዎች ስለቀረቡ እና በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገቦች ተቃውሞ የቀረበበት ስለሆነ ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች የሚያነሱት ክርክር ቤቱን ሟች ከአሁን 1ኛ አመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ እያሉ ያፈሩት በመሆኑ የአሁን ተጠሪዎች አይመለከታቸውም የሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በበኩላቸው ከ1965 ዓ/ም ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ እና ሟች እንደ ባልና ሚስት ከዚያ በኋላ ከ1972 ዓ/ም ጀምሮ ህጋዊ ጋብቻ መስርተው ያፈሩት ንብረት እንደሆነ እና በኑዛዜ የተላለፈላቸው በመሆኑ አመልካቾችን አይመለከታቸውም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ ሟች በሕይወት እያሉ ያደረጉትን ኑዛዜ ውድቅ በማድረግ፤ በሟች ስም ተመዝግቦ ባለው ቤት ላይ ወ/ሮ መሰለች ታደሰ በንብረት ተጋሪነት ቢመዘገቡም ሟች ከመዘገቡ እንዲወጡ አቤቱታ ሲያቀርቡ መቆየታቸውን በማረጋገጥ የንብረቱ ተጋሪ ሊሆኑ አይገባም ብሎ ወስኗል፡፡ በመቀጠል የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሟች ጋር ከ1965 ዓ/ም ጀምሮ እንደባል እና ሚስት ሲኖሩ መቆየታቸውን የገለጹ ሲሆን በውርስ አጣሪ ቀርበው ጥቅምት 19 ቀን 1962 ዓ/ም የተፈጸመ የባህል ጋብቻ ማቅረባቸው ከክርክራቸው ጋር እርስ በእርስ የሚጋጭ ነው፤ ሌላው በቀረቡት ምስክሮች ቃል ሟች ከስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ጋር በ1973 ዓ/ም ጋብቻ ፈጽመው በሀገር ባህል መሰረት ሲኖሩ እንደነበር የመሰከሩ በመሆኑ ይህ ምስክርነት በሌላ ምስክር ቃል የተደገፈ መሆኑ ሲታይ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበው የሀገር ባህል ጋብቻ ማስረጃን አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት እንደ ባል እና ሚስት ስንኖር ነበር በሚል የተነሳውን ክርክር እና ያቀረቡትን ማስረጃ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ስለሆነ የሀገር ባህሉ ጋብቻ ማስረጃው ይዘት ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የባህል ጋብቻ መስከረም 15 ቀን 1973 ዓ/ም የተፈጸመውን የባህል ጋብቻ በ18/05/2002 ዓ/ም መመዝገቡን የገለጹበትን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ተቀብሏል፡፡ ሌላው ነጥብ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከቀረቡት ምሰክሮች ቃል መረዳት እንደሚቻለው ሟች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ወቅት መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ እድሳት መደረጉ ነው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 94952 ንብረቱ የጋራ ሀብት እንደሚሆን የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የሟች ሀብት ተጋሪ ናቸው ተብሏል፡፡ በመሆኑም በአስተዋጾ ረገድ በስር ፍርድ ቤት በ1ኛ ተጠሪ በኩል የተነሳ ክርክር ባለመኖሩ ንብረቱን 1ኛ አመልካች፣ ወራሾች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የቤት ኪራይ ገቢን በተመለከተ የ2ቱ ክፍሎች ኪራይ ዋጋ ብር 1,600 ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ የስር ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች፣ 1ኛ ተጠሪ እና ወራሾች እያንዳንዳቸው 1/3 ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ በኢትዮጲያ ንግድ ባንክ ከሚገኘው ገንዘብ ሟች ካረፉ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ብር 58,500 ማንቀሳቀሳቸው ስለተረጋገጠ የእሳቸው ዕዳ ሆኖ የገንዘቡን 1/3ኛ ለስር ፍርድ ቤት አመልካች፤ 1/3ኛውን ለወራሾች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች፣ ሟች እስከ እለተ ሞታቸው በጣታቸው የሚያጠልቁት 20 ግራም ወርቅ በማለት ያቀረቡትን ዳኝነት በተመለከተ በማስረጃም ሆነ በሌላ መልክ ያላስረዱ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ አብሮ አደግ (መተባበር) የህብረት ሥራ ማህበርን በተመለከተ የውርስ ድርሻ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የለም በዚህ የህብረት ሥራ ማህበር ቁጠባ ብድር ውስጥ በስር ፍርድ ቤት በ1ኛ ተጠሪ ስም ሟች አስከሞቱበት እስከ 18/12/2009 ዓ/ም ድረስ የተቆጠበው ብር 2,830 መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ካቀረቡት የአባል የሒሳብ ደብተር ላይ ስለተመዘገበ በውርስ ሀብትነት ተመዝግቦ 1ኛ አመልካች፣ 1ኛ ተጠሪ እና ወራሾች እያንዳንዳቸው 1/3ኛ ድርሻ አላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በኩል በሟች ስም በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በጋሞ ጎፋ ዞን በጨንቻ ወረዳ የሚገኝ ቤት፣ የእርሻ እና የሳር መሬት፣ የቤት እንስሳት እና ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በተመለከተ ተቃውሞ የቀረበበት አይደለም፤ የቤት ኪራይን በተመለከተ ተቃውሞ የቀረበበት ሲሆን በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪን በተመለከተ ከእድር ወስደዋል የተባለውን ገንዘብ ከግምት በማስገባት የበሬ፣ የተለያዩ የምግብ ሥራ ወጪዎች ስለተረጋገጡ ብር 20,000 የውርስ ዕዳ ሆኖ የስር ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች፣ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ እና ወራሾች 1/3ኛ ድርሻ ይሸፍኑ ተብሎ ተወስኗል፡በ19/06/2013 ዓ/ም ተሻሽሎ የቀረበው የውርስ ሪፖርት ከላይ በተዘረዘረው መልክ ተሻሽሎ እንዲጸድቅ፤ ሪፖርቱ ህግን እና መልካም ጸባይን የማይቃረን፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 944ን መሰረት አድርጎ የተጣራ ስለሆነ እንዲጸድቅ ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን እና መስቀለኛ ይግባኙን መርምሮ ከውርስ ሀብቱ ላይ የኑዛዜ ተጠቃሚ የለም በማለት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሟች ጋር በነበራቸው የትዳር ዘመን ቤቱ መታደሱ እና መሠራቱን፤ መሰረታዊ ለውጥ በቤቱ ላይ መደረጉን በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡዋቸው ምስክሮች እና ማስረጃዎች አስረድተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የነበራቸውን የተለየ አስተዋጾ አረጋግጦ ባለበት ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤ/ቁ 096 የተመዘገበው ቤት እና ከቤቱ የሚገኘው ኪራይ ላይ ከሟች ጋር ያፈሩት ባደረጉት አስተዋጾ ልክ ድርሻቸው 50 % ሊሆን ይገባል የአሁን 1ኛ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ድርሻ ላይ እኩሌታ 25 % ድርሻ ተካፋይ ሊሆኑ ይገባል፤ ቀሪው የሟች ወራሾች ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡ በደቡብ ክልል ጋሞ ጎፋ ዞን ዶርዜ ከተማ እና ደቡብ ክልል ጨንቻ ወረዳ ያሉ የውርስ ንብረቶች የእርሻ ባህርዛፍ እና ቤቶች ሟች ከአሁን 1ኛ አመልካች ጋር በነበራቸው የትዳር ዘመን ያፈሩት መሆኑ ያላከራከረ ስለሆነ የአሁን 1ኛ አመልካች በነበራቸው የትዳር ዘመን የራሳቸውን አስተዋጾ በማድረግ ንብረቱን ስለማፍራታቸው ግምት ስለሚወሰድ የአሁን 1ኛ አመልካች 50 % ድርሻ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሊያገኙ ይገባል፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሟች የውርስ ንብረት 25 % ተካፋይ ሊሆኑ ይገባል፤ ቀሪው የሟች ወራሾች ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለቀብር እና ተያያዥ ወጪዎች ብር 20,000 አውጥተዋል ብሎ ከወሰነላቸው በኋላ ይህንኑ ከአሁን 1ኛ አመልካች እና ከወራሾች ከሚገኝ ድርሻ ላይ ተቀንሶ ሊከፈላቸው፤ ሊታሰብላቸው የሚገባ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያወጡትን የወጪ ልክ አመዛዝኖ ከወሰነ በኋላ መልሶ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ዕዳውን ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ለቀብር ማስፈጸሚያነት የከፈሉት ብር 20,000 በውርስ ዕዳነት ተይዞላቸው ከሟች ወራሾች እና ከአሁን 1ኛ አመልካች ድርሻ ላይ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡ የአሁን 1ኛ አመልካች የሚጠቅሷቸው ወ/ሮ መሰለች ከሟች ጋር ህጋዊ ጋብቻ ወይም የትዳር ሁኔታ እንዳላቸው በተጨባጭ ባላስረዱበት ሁኔታ ከህግ ወይም ከውል በፍርድ ውሳኔ ከሟች ጋር ትዳር እንደነበራቸው ባልተረጋገጠበት ሟች ከአሁን 1ኛ ተጠሪ እና ከአሁን 1ኛ አመልካች ጋር በትዳር ዘመናቸው ያፈሩዋቸውን ንብረቶች በህግ ተከራክሮ ለማግኘት የሚያስችላቸው ቀድሞ የተፈጠረ መብት እንዳላቸው ሳይረጋገጥ የሟች 3ኛ ሚስት ናቸው የንብረቱም ተጋሪ ሊሆኑ ይገባል በማለት የአሁን አመልካቾች የሚያቀርቡት መከራከሪያ የማስረጃም ሆነ የህግ ድጋፍ የሌለው ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ አክሊሉ እና ዘሪሁን የብሎኬት ማምረቻ የህ/ሥ/ማህበር በአባልነት የመዘገበው የአሁን 1ኛ ተጠሪን ሆኖ ሳለ በማህበሩ ላይ የሚደረገውን መዋጮ ሟች ያደረጉት ስለመሆን አለመሆኑ ማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ ማህበሩ ሟችን በማህበር አባልነት መዝግቦ ባልያዘበት በቀጥታ የቁጠባ ማህበሩ ላይ ያለው ብር 2,830 በግልጽ የ1ኛ ተጠሪ መብት በሆነበት አግባብ የውርስ ድርሻ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፤ በቁጠባ ማህበሩ ላይ ያለው መብት ድርሻ የ1ኛ ተጠሪ መብት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ማህበሩ ላይ የሚገኝ ማንኛውም መብት ሆነ የሟች ድርሻ በገንዘብ ወደፊት ሊለይ እና ሊታወቅ የሚችል ከሆነ በተለይም የተጠቀሰው ማህበር ባቋቋማቸው አዋጅ እና ህግ መሰረት ወራሾች ሊያገኙ ሊተላለፍላቸው የሚችል መብት ወደፊት ሊገኝ የሚችል ከሆነ የሟች ህጋዊ ወራሾች ይህንን መብት እና ጥቅም ከማህበሩ ላይ የማህበሩ ህገ-ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ከመጠየቅ ሊከለከሉ ስለማይችሉ የስር ፍርድ ቤቱ በደፈናው ከማህበሩ የውርስ ጥቅም ሆነ ገንዘብ የለም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ስላልሆነ ወደፊት የሚተላለፍ ጥቅም ትርፍ ክፍፍል ካለ ግራ ቀኙ ወደ ፊት የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል ተብሎ ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል በሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ከኪራይ የሚገኝ ገቢን አስመልክቶ፣ ሟች አድርገውት የነበረው ቀለበት አስመልክቶ እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን በተመለከተ ያቀረቡትን አቤቱታ ባለመቀበል በመሰረዝ ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 03 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ያለበት ስለሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለማስለወጥ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የተጋሪነት ድርሻ መጠን ለመለየት የተደረገውን አስተዋጾ፣ በንብረቱ መገኘት (መፈራት) ላይ ያበረከቱትን ጥቅም ያለው የዋጋ መጠን ማመዛዘን ያለባቸው ስለመሆኑ የፌዴራል የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች ያስገነዝባሉ፡፡ በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወረዳ 12 የሚገኘውን የቤ/ቁጥር 096 በማፍራት ተጋሪ የሆኑት የሟች ሚስት የ3ኛ አመልካች እናት ወ/ሮ ደንገርሴ ደጋጋ ስለሆኑ የንብረት ተጋሪነት መብት እና ጥቅም የልጃቸው የ3ኛ አመልካች ነው፡፡ ወ/ሮ ደንገርሴ በ1962 ዓ/ም ከሞቱ በኂላ አቶ ከተማ ጨንጎ ወ/ሮ መሠለች አባመስጠት/ታደሰ/ ያገቡ ሲሆን ወ/ሮ መሠለች ያላቸውን ድርሻ በኑዛዜ ለ3ኛ አመልካች አውርሰዋል፤ የስር ፍርድ ቤት ግልጽ በሆነ ስህተት (ክርክር የማጣራት ግድፈት) ይህ ኑዛዜ ተሸሯል በማለት ፍርድ የሰጠው በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ባልቀረበ ክርክር ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የተሰረዘው ኑዛዜ ሟች ከተማ ጨንጎ የሰጡት ኑዛዜ እንጂ ለ3ኛ አመልካች የተደረገው ኑዛዜ አይደለም፡፡ የሟች ሚስቶች ከነበሩት ከወ/ሮ ደንገርሴ ደጋጋና ከወ/ሮ መሰለች ታደሰ ጋር ሟች ያፈሩትን በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወ/12 የሚገኘውን የቤ/ቁ 096 የሆነውን ቤት የሟች ድርሻ 25 % (1/4ኛ) ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከ2ኛ-8ኛ የተመለከትነውን አመልካቾች በእጅጉ የጎዳ እና ሟች 1ኛ ተጠሪን ከማግባታቸው አስቀድሞ ከሌሎች 2 ሚስቶቻቸው ጋር ንብረቱን ለማፍራት ያደረጉትን አስተዋጾ ስሌት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ስሌቱ የንብረቱን መፈራት ስሌት ያላካተተ እና የዕድሳት አስተዋጽኦ መጠንም በባለሙያ ሳይጣራ እና ሳይሠራለት የተሰጠው የ1/2ኛ ተጋሪነት ድርሻ ፍርድ መሰረታዊ ስህተት ነው ሊባል ይገባዋል፤ ሟች ለዚህ ንብረት መፈራት ከ1954 ዓ/ም ጀምሮ ያፈሩት ንብረት በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪ ምንም አስተዋጾ ያላደረጉ ስለሆነ ምንም ድርሻ ሊሰላላቸው አይገባም፡፡ የአሁን 1ኛ አመልካች እና ሟች የትዳር ዘመን ከ1965 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሟች ዕለተ ሞት ድረስ መሆኑ ከዕድሳት በፊት በነበረው የንብረት እሴት 50 % ይገባቸዋል፡፡ ዕድሳት በሚፈጸምበት ጊዜ የጋራ እና እኩል አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆኑ በተለይም ተደርበው ሚስት የሆኑ (በኂላ ሟችን ያገቡዋቸው) የአሁን 1ኛ ተጠሪ በመሆናቸው በዚህ ቤት ላይ 1ኛ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች የበለጠ ድርሻ እንዲኖራቸው መወሰን የሰበር ውሳኔዎችንም ሆነ የቤተሰብ ህግ ዓላማን የተጻረረ ነው ተብሎ ፍርድ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የድርሻ ክፍፍልን በተመለከተ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ 1/2ኛ ሊሆን አይገባም፤ በዚህ ንብረት አንጻር 1ኛ ተጠሪ በዕድሳት ላበረከቱት አስተዋጽኦ የአስተዋጽኦ መጠን 50 % በገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል፤ 1ኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 47/67 ድንጋጌ እና በዕድሳት ሂደት ጊዜም የነበሩ መሆናቸው አከራካሪ ባለመሆኑ ተመጣጥኖ 25 % ድርሻቸው ነው ተብሎ እንዲታረም እና የ3ኛ አመልካች የኑዛዜ አውራሽ እና የወላጅ እናቱ የወ/ሮ ደንገርሴ ደጋጋ የወ/ሮ መሰለች ታደሰን ድርሻ 25 % ሊሆን ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልን።

በደቡብ ክልል ጋሞ ጎፋ ዞን ክልል ውስጥ የሚገኙ የውርስ ንብረቶችን በተመለከተ የውርስ ንብረቶች ከማፍራት አንጻር 1ኛ ተጠሪ ያደረጉትን አስተዋጾ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ በሌለበት እና ሟች እና 1ኛ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ እና ሟች ትዳር አስቀድመው ባፈሩዋቸው ንብረቶች ላይ የተጋሪነት መብት ሳይኖራቸው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበውን ክርክር እና በማስረጃ ያልተረጋገጠን ጭብጥ በመያዝ 1ኛ ተጠሪ 25 % ድርሻ ይገባቸዋል በማለት የሰጠው ፍርድ እንዲሻርልን፤ የእነዚህ ንብረቶች 50 % የ1ኛ አመልካች መሆኑ እንዲጸና እና 50 % የሟች ድርሻ ነው ተብሎ ተሻሽሎ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ በዚህ ጉዳይ ሟች የ4 ሚስት ባለቤት በሆኑበትና ጋብቻውንም የፈጸሙት በተለያየ ጊዜ በሆነበት እና ንብረቱም የተፈራው በተለያየ ጊዜ በሆነበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የንብረት ክፍፍሉን ሲወስኑ የሚስቶቹ አስተዋጽኦ ማየታቸው እና አለማየታቸው ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል።

ተጠሪዎች ግንቦት 10 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የመከላከያ መልስ ሟች ነሐሴ 18 ቀን 2009 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በደቡብ ክልል ውስጥ 1ኛ አመልካች እና አዲስ አበባ ውስጥ ላለፉት 50 ዓመታት ገደማ የትዳር አጋራቸው ከሆኑት ከ1ኛ ተጠሪ ውጪ ሌላ ሚስት የነበራቸው ስለመሆኑ ለውርስ አጣሪም ሆነ ለፍርድ ቤት በህጉ አግባብ የቀረበ ጉዳይ የለም። አመልካች በ1954 ዓ/ም የተፈራ ንብረት ነው የሚሉት የህዝብ እና የመንግስት የሆነውን ሟች የተመሩትን የመሬት ይዞታ ነው። አመልካቾች ምንም ዓይነት ህጋዊ አካሄድ ሳይከተሉ 4 ሚስቶች ያሉ በማስመሰል ድርሻቸው ይወሰንልን በሚል ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የለም። 3ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ጋር በነበረ ትዳር የተወለዱ ስለመሆኑ 3ኛ አመልካች በሥር ያቀረቡት የወራሽነት ማረጋገጫ ያሳያል። 1ኛ ተጠሪ በነበረው አነስተኛ ጭቃ

ቤት ላይ ጥረው ባገኙት ገቢ መሰረታዊ ለውጥ በማድረግ ፍጹም አዲስ እና ሌሎች ቤቶች በመገንባት ቀድሞ የተሠራበትን ዕቃ እና ቅርጹን በመቀየር መገንባታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 219887፣ 50489 እና 45548 አንጻር አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ተብሎ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸናልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ሰኔ 05 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ ከወ/ሮ ደንገርሴ የተለወዱትና ወ/ሮ መሰለች አባመስጠት/ታደሰ/ በኑዛዜ ያወረሷቸው 3ኛ አመልካች ሳይሆኑ 7ኛ አመልካች መሆናቸውን በመግለጽ እና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ ተጀመረው የሚች ከተማ ጨንጎ የውርስ ሀብት ለማጣራት በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሀብቱ የተጣራ ሲሆን ግራቀኙ ያቀረቡትን አስተያየት በመቀበል ክርክርና ማስረጃ በመስማት የውርስ ሀብቱ ወራሾች እና ድርሻቸውን የመለየት ሥራ ተከናውናል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፡፡ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም ምክንያትን ማስፈር እንደሚገባ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 182(1) የተመለከተ ግዴታ ነው፡፡ ፍርድ በሚጻፍበት ጊዜ

ማሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስለጉዳዩ መግቢያ፣ በክርክሩ የተነሱትን ፍሬ ነገሮች ማስፈር፣ ምላሽ የሚያስፈልገውን የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ጭብጥ መለየት፣ በተለየው ጭብጥ ማስረጃውን በመመዘን እና ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ በመተግበር ለውሳኔው ምክንያትን በማስፈር ዳኝነት የተጠቀበትን ጉዳይ እልባት መሥጠትን ይጠይቃል፡፡ በዚህም ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ፣ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ዳኛው ሕጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ያነሱት የሟች ሚስት የነበሩት ወ/ሮ መሰለች አባመስጠት/ታደሰ/ በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸውና ድርሻቸውን በኑዛዜ ለ3ኛ አመልካች ያስተላለፉ ስለመሆኑ ከገለጹ በኋላ በመልስ መልሳቸው ኑዛዜ የተደረገው ለ7ኛ አመልካች ነው በማለታቸው ማቅረባቸው ግልጽነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልጽ እንደሰፈረው በቀረበው ክርክርና ማስረጃ የተረጋገጠው ሟች ከተማ ጨንጎ 1ኛ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አግብተው መኖራቸው ነው፤ ከዚህ ውጭ ሌላ ሚስት የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፣ ወ/ሮ መሠለች ሚስት የነበሩ ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ ደግሞ በሟች ከተማ ጨንጎ ንብረት ላይ ድርሻ መብት ስለማይኖራቸው ድርሻ አለኝ በሚል ሃሳብ ያደረጉት ኑዛዜ ቢኖር እንኳን መብት የማያስተላልፍ ዋጋ አልባ ነው፤ ስለሆነም በሥር ፍርድ ቤቶች ሚስትነታቸው የተረጋገጠውን የ1ኛ አመልካች እና የ1ኛ ተጠሪን ድርሻ እንዲሁም የሟች ከተማ ጨንጎን ወራሾች በመለየት ድርሻ መወሰናቸው ተገቢ ነው፡፡

አመልካቾች አዲስ አበባ ከተማ ስለሚገኘው ቤት እና ጋሞ ጎፋ ዞን ስለሚገኘው ንብረት ድርሻ ክፍፍል በተመለከተ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ሲሆን ውሳኔውን ያሻሻለው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በየትኛው ንብረት የትኛዋ ሚስት ንብረቱ በመፈራቱ ረገድ ያላቸውን አስተዋጽኦ በመለየትና ግምት ውስጥ በማስገባት ድርሻቸውን የለየ ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ውሳኔው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ቤት 1ኛ ተጠሪ ያላቸውን አስተዋጽኦ መሠረት በማድረግ የቤቱ ግማሽ ባለድርሻ መሆናቸው እንዲሁም ጋሞ ጎፋ ዞን በሚገኘው ንብረት 1ኛ አመልካች ያላቸውን አስተዋጽኦ መሠረት በማድረግ ግማሽ ባለድርሻ ማድረጉ የቀረበውን ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስቀተር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 282101 ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !